# የኢትዮጵያ ሕዝብ፣ አገር-ወዳድና ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች እና ኢሕአዴግ፤ <u>ከዚኽ ወዴት</u>?

*ከአያል ሰው ደሴ፤- የግል አስተያየት*

***<u>ክፍል አሥር</u>*** *<u>(ከክፍል ዘጠኝ የቀጠለ)፤-...</u>*

በመሆኑም፣ ምንም እንኳን በሁሉም ዘንድ በጎ-ፈቃድ ሊኖር ቢችልም፣ በአንድ በኩል "ተባባሪ-አባል" በተባሉት (በአብዛኞቹኛው ፖለቲካዊ ባልሆኑ ስብስቦች) እና በኢሰዴአኃ፤ በሌላ በኩል ጉባዔውን ባዘጋጁትም ይሁን ኢሰዴአኃን በመሠረቱት ዋና ዋና በተባሉት "አባላት" እና በኢሰዴአኃ (በአመራሩ) መኻል አለመጣጣሞችና ቅራኔዎች ብቅ ብቅ ማለት ሲጀምሩ ጊዜ አልወሰዱም:: በምክር-ቤቱ አንደኛ ዓመት ዘገባ ላይ እንደተጠቀሰው በወቅቱ ኢሰዴአኃ በአባልነት ካቀፋቸው በአገር-ውስጥና ከአገር-ውጭ ከሚገኙ አምሣ-አንድ አባል ድርጅቶች በኩል ከተሣትፎ ጀምሮ ልዩ ልዩ ኃላፊነቶችን መወጣት አለመቻል፣ የድርጅት ተወካዮች አለመታመን፣ ምስጢር የማባከንና የክዳት ተግባሮችን መፈጸም፣ ከመተዳደሪያ-ደንብና ከአባል ሥነ-ሥርዓትና ደንብ ውጭ በሆኑ መንገዶች ተፃራሪ ተግባሮች ላይ መሠማራት፣ ለምክር-ቤቱ ሣያስውቁ እራሣቸውን ማግለል፣ ወዘተ.. የመሣሰሉ ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ገጥመውታል:: የኢሰዴአኃ ምክር-ቤት አደረጃጀትና አወቃቀር የፈጠራቸው ችግሮችም እየተበራከቱና ከሌሎች ጋር ተዳምረው ወቅታዊ መፍትኄዎች ሳያገኙ በመቀጠላቸው ሌሎች አባላቱን አራግፎና የደቡብ ኅብረትን ብቻ በአባልነት ይዞ እንደየሁኔታው አንድም ሁለትም በመሆን እስከ ምርጫ-ዘጠና-ሰባት ስሙን ብቻ ተሸክሞ እንዳዘገመ ይታወቃል::

*<u>ለ) የትግል መሥመርና ትልም (ስልትና ስትራቴጂ)፤-</u>* እንደሚታወቀውና ቀደም-ሲልም እንደተገለፀው አማራጭ ኃይሎች ሲመሠረት ፈር-የለቀቀውንና ሕወሓት/ኢሕአዴግን ከሽግግር መንግሥትነት ወደ-ቋሚ መንግሥትነት በማዘዋወር የሕዝባችንን የዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለውጥ የጋለ ፍላጎት ጨርሶ ወደሚያከስም አቅጣጫ እያመራና አገሪቱን ለአንድ ድርጅት ፍጹም የአምባ-ገነን ፈላጭ-ቆራጭ የአገዛዝ ሥርዓት እያመቻቸ የነበረው የአገሪቱ ሁኔታ ተገትቶ፣ በምትኩ በተቃዋሚው ጎራ የተሰለፉትን ኃይሎች በአጭሩ "ለአዲስ ዴሞክራሲያዊ ጅማሮ" በሚል መፈክር ሥር በማሰባሰብና በአንድ የጋራ ትግል መድረክ ሥር በማደራጀት ሕዝባዊና ሰላማዊ የጋራ ትግሉን መሥመር ለማስያዝ ነበር:: ለዚኽም ኢሰዴአኃ የለውጥ ፈላጊውን ዴሞክራትና አገር-ወዳድ ኃይል ትኩረት በማሾርና በአንድ አቅጣጫ እንዲሰለፍ በማድረግ፣ ሁሉም ኃይሎች ተሣታፊ ከሚሆኑበት አገራዊ የሰላምና እርቅ የሚመነጭ አዲስ የሽግግር ሂደትን በመከተል የአምባ-ገነኖች አዙሪት እንዲያከትም፣ ሕዝባችን የሥልጣኑ ባለቤት መሆኑን በተግባር የሚያስረግጥበትና ኅብረተሰባችንን በአጠቃላይ ከአምባ-ገነንና ከኢ-ዴሞክራሲያዊ የአገዛዝ ሥርዓት ወደ ዴሞክራሲያዊና ሕገ-መንግሥታዊ ሕዝባዊ ሥርዓት የሚያሸጋግር <u>ሁኔታን ለማመቻቸት</u> አልሞ የተነሣው ፈታኙንና ለጊዜው አስቸጋሪውን ግን ውጤቱ አስተማማኝና ዘለቄታዊ ሊሆን የሚችለውን ሰላማዊ የትግል ስልት መርጉ አድርጎ በመያዝና በመከተል ነበር::

ሆኖም ግን ኢሰዴአኃ ሲመሠረት ይኽ ሂደት ከምኞታዊነት በዘለቀ ተግባራዊ እንዲሆን በአባላት ዘንድ በሂደቱ ላይና ግቡን ለመጨበት የሚኖረውን ውስብስብ ችግር በተገቢ ባጤነ መልኩ መራር ትግሉ በተጨባጭ በሚጠይቀው ሁለንተናዊ ዝግጁነትና ከእያንዳንዱ በተናጠልና በወል የሚጠበቅ አስተዋፅዖ ላይ ግልጥ መግባባትና ስምምነት ነበር ማለት አይቻልም:: በተለይም መሠረታዊ የሆኑ የዴሞክራሲ እሴቶች በልተረጋገጡባት ኢትዮጵያ፣ እንደ ኢሕአዴግ መሪዎች ዓይነት ለሕዝብና ለታሪክ ከበሬታ፣ ለሰብዓዊ መብትና ለሕግ የበላይነት መከበር ደንታ ከሌላቸው፣ በአጉል ትዕቢትና እብሪት ከተወጠሩ አፍላ ጉልበተኞች ጋር የሚደረግ ሰላማዊ ትግል ፈታኝነትና ያንን ለመቋቋም የሚጠይቀውን

ጥንካሬና አንድነት ላይ በሁሉም አባላት ዘንድ የጠራ ግንዛቤ አለመኖር በአንድ በኩልና እነኝኽ "ለብሔር/ብሔረ-ሰብ እና ሕዝቦች" መብት ቆመናል ባይ ተቀጣጣቢዎች በአገሪቱ ላይ አነሁላይ የፖለቲካ ውኸ‍ንብር ባሰፈኑበት፣ ስለ አገራዊ አንድነትና ስለ ሕዝብ የጋራ መጻዒ-ዕድልና ኀልውና መቆም በተዛባ መልኩ እንደ "ያለፈ ሥርዓት-ናፋቂና ትምክኀተኝነት" ተደርጎ በተወሰደበት፣ ሕዝባችን ሦስት አሥርተ-ዓመታት የጦርነት ሰቆቃ ገና ከአእምሮው ባልጠፋበትና የማገገሚያ መንገዱን ለመያዝ በሚባዝንበት፣ መረጋጋት ጨርሶ ባልተረጋገጠበጥ፣ ኀብረተሰቡ በስፋት አዲሶቹ ገዥዎች የሚነዙትንና የሚሰብኩትን "ለእኩልነትና ለዴሞክራሲ ሥርዓት" መቆም ባዶ ጩኸት ከእውነተኛ ኢ-ዴሞክራሲያዊ ድርጅታዊ ባኅሪያቸውና ገፅታቸው ለይቶ ለማየትና በደንብ ለማወቅ ባልቻለበት የተወናበደ ሁኔታ ስብጥርጥሩ የወጣውን ኃይል አንድ ላይ አሰባስቦ የሚደረግ የጋራ ፍልሚያ ቀላል እንዳልሆነ በሁሉም ዘንድ ተመሣሣይ ቀርቶ ተቀራራቢ ግንዛቤ እንዳልነበር ይታወቃል።

ያም በመሆኑ በዚያ ዓይነት ፈታኝ ሁኔታ ለሚደረግ ወሳኝ ፍልሚያ የሚቋቋም የኃይሎች መሰባሰብ አመራሩ፣ አካሄዱ፣ ግቡና የትግል ስልቱ ጥርት ያለና ምንም አሻሚነት የሌለው ሊሆን ተገቢ ሲሆን፤ ይኽንን ለማድረግ ደግሞ ትግሉን በሚመሩት ዘንድ ልዩ መንፈሣዊ ጥንካሬን፣ አስፍቶ-ማየትን፣ የፖለቲካ ብስለትንና ወሳኝነትን የሚጠይቅ መሆኑ ግልጥ ነው። በዚኽ ረገድ በልምድ እጥረትም ይሁን የወቅቱ የጎሠኝነት/ጎጠኝነት የፖለቲካ አየር በፈጠረው አጠቃላይ የውኸ‍ንብር ሁኔታ ምክንያት በኢሰዴአኃ በኩል ትልቅ ክፍተት ነበር ማለት ይቻላል። በተጨማሪም በተወሰኑ ለውጥ ፈላጊ ኃይሎች ዘንድ የደርግ አስከፊ ሥርዓት መወገድን ተከትሎ በተለይ የውጭ ኃይሎች አዲሶቹን ገዥዎች ማሽበልበላቸውን፣ ማሞካሸታቸውንና እንበለ-ማጠየቂያ ጭፍን ድጋፋቸውን መለገሣቸውን በሌጣው በመውሰድ እነዚኽ ኃይሎች የሰብኣዊ መብቶች መከበርን በመሣሰሉ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ መሠረታዊና ቁልፍ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ኢሕአዴግ የተሻለ ይዞታ እንዲኖረው ጫና ሊያሳድሩ ይችላሉ የሚል ብዥታ የተስተናገደበትና በዚያም ምክንያት ሙሉ ትኩረታቸውንና ጥረታቸውን የለውጥ ዋነኛ አንቀሣቃሽ በሆነው ሕዝባችን ላይ በማድረግ ፋንታ በተዛባ መልክ በውጭ ኃይሎች አሸማጋይነትና ጫና የማድረግ ችሎታ ላይ አጉል አመኔታ ማሳደራቸው በትግሉ ላይ አሉታዊ ተፅዕኖ ነበረው የሚል እምነት አለኝ።

በኢሰዴአኃ አባል ድርጅቶች መካከል ከልብ ያለ-መግባባትና ያለ-መተማመን በመኖሩም የተወሰደው የትግል ስልት እንዲሰምር የሚጠይቀውን ሙሉ ትኩረትም ሆነ የሚጠበቀውን ቀና ተሣትፎ ከአባላቱ ሊያገኝ አልቻለም። ከሁሉም በላይ ግን ቅድመ-አማራጭ ኃይሉም ሆነ ከዚያ ወዲኽ በተደጋጋሚ እንደታየው በሁሉም የምክር-ቤቱ አባላት ዘንድ በራሱ በሰላዊ ትግል ጽንሰ-አሳብ ላይ በተገቢ መግባባት የነበረ አይመስልም። ይኽ ጥያቄ በአንደምታና በደፈናው የተወሰደ እንጂ በተገቢ ውይይት ያልተደረገበትና ሙሉ መግባባት ላይ ያልተደረሰበት በመሆኑም በለውጥ ፈላጊው ወገን እስከ-አሁን ድረስ የዘለቀ ከፍተኛ የሆነ ጥልቅ የግንዛቤ ፍልሰት የወለደው ችግር እንዳለ ግልጥ ነው። አንደኛ ነገር በብዙ ወገኖች ዘንድ በተደላደለ ሁኔታ ማለትም የሕግ የበላይነት በተረጋገጠበት፣ ሰብኣዊ መብቶች በተከበሩበትና ዴሞክራሲያዊ እሴቶች እውን በሆኑበት አገር በሚደረግ አዘቦታዊ ሕጋዊ ሰላማዊ ትግል እና እንደ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ከመሰለ ከፍትኀ ጋር ትውውቅ ከሌለውና የአሣብ ልዩነትን የማስተናገድ ፖለቲካዊ ባኀል ጨርሶ ከሌለው አፋኝ አምባ-ገነን የአገዛዝ ሥርዓት ጋር የሚደረግ ሰላማዊ ትግል መኻል ያለው ልዩነት ላይ እራሣቸው ለለውጥ በቆሙ ድርጅቶች ውስጥ ከፍተኛ ብዥታ አለ። ያ መሠረታዊ የግንዛቤ ጥራት ችግርም እስከ-አሁን ድረስ ትግሉን ያሽመደመደ፣ ታጋዩ ሕዝባችንን ለአጉል መስዋዕትነት የዳረገና ተስፋውን ያቀጨጨ እንደሆነ ሊታወቅ ይገባል። <u>የሕግ የበላይነት በሌለበትና ዴሞክራሲያዊ እሴቶች ባልዳበሩበት አገር ከአፋኝ የአገዛዝ ሥርዓቶች ጋር የሚደረግ ሰላማዊ ትግል፣ ግብ እንዲመታ ከተፈለገ ሰላማዊ ብቻ ሣይሆን የግድ ሕዝባዊም መሆን ይኖርበታል።</u> ለብዙዎች ሰላማዊ ትግል ሲባል የአገዛዙን "ሕጋዊነት" የተከተለና አገዛዙ የፈቀደውና በፈቀደው መንገድ ብቻ የሚደረግ ተደርጎ ይወሰዳል። ይኽ ደግሞ በገቢር የሥርዓቱ ትዕዛዝ-ፈጻሚ ከመሆን ያልዘለለና በስም ካልሆነ በስተቀር በተግባር አገዛዙ ባኀሪውን እንዲቀይር የሚያስገድድ እርባና ያለው ትግል ለማድረግ ፈጽሞ የማያስችል ነው።

በሰላማዊ ትግል ይዘት ላይ እዚኽ የማቀርበው አጭር አስተያየት በአንዳንድ ወገኖች ዘንድ “ለተቀማጭ ሰማይ ቅርቡ ነው” እንዲሉ ዓይነት ተወስዶ ምናልባት 'በቦታው ላይ ስለሌለህ ይሆናል፣ በአገሪቱ “ሕግ” ሥር እስካለን ድረስ የምናደርገው ትግል እስካሁን ከተከተልነው ውጭ ሊሆን አይችልም' ሊባል እንደሚችል እገምታለሁ፡፡ ጉዳዩ ቀላል የአመለካከት ልዩነት ሣይሆን መሠረታዊ የመርኅና የግንዛቤ ጥያቄ ስለሆነ፣ እንዲሁ በደፈናው “አልተግባብቶም” ተብሎ ሊታለፍ የሚችል አይደለም፡፡ ይኽ ዓብይ ጉዳይ ላይ ግልጥና ጥልቅ ውይይት ባለመደረጉ፣ በተለይ በዘመነ-ሕወሓት/ኢሕአዴግ አንዳንድ ወገኖች ከአንድ አጥናፍ ወደ-ሌላ አጥናፍ ሲወናጨፉና ትግሉን የስሜቶች መግሪያና መፈተኛ ማድረጋቸውን በአግራሞት ስናይ እነሆ ረጅም ጊዜ አስቆጥረናል፡፡ እዚኽ ላይ በኢሰዴአኃ አባል ድርጅቶች መኻል በሰላማዊ ትግል ጽንሰ-አሣብ ላይ የጠራ ግንዛቤ አለመኖሩ ለምክር-ቤቱ ውድቀት ቀጥተኛ አስተዋፅዖ ማድረጉ ሲነገር አንዳንዱ በወቅቱ በቀና መንፈስ ለትግሉ ግብ መምታት ያደረገውንና የከፈለውን ከፍተኛ መስዋዕትነት በመዘርዘር ንዴቱንና ቁጭቱን ማሰማቱ አይቀርም፡፡ ከዚያ በፊት ግን ለነዚኽ ወገኖቸ ግልጥ ማድረግ የምፈልገው በታጋዩ ሕዝባችን፣ በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያና በሌሎች ቦታዎች በሚገኘው ሕዝብ እንዲሁም በአንዳንድ የኅብረተሰባችን ክፍሎች ለዜጎች መብትና ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት እውን መሆን የተከፈለውን ከፍተኛ መስዋዕትነት በክብር ከፍ ተደርጎ እንዲታይ ከማድረግ ውጭ በምንም ዓይነት እንዳልነበር ሊቆጠርም ሆነ ሳይዘከርና ተገቢውን የአክብሮት እውቅና ሣይሰጠው መታለፍ የለበትም ባይ ነኝ፡፡ ያ ታሪክ ደግሞ ምን ጊዜም በመላ የኢትዮጵያ ሕዝብ ልብ ውስጥ ተቀርፆ እንደሚቀመጥ እምነቴም፣ ተስፋየም ነው፡፡ ቁም-ነገሩ በተወሰኑ የአገሪቱ ክፍሎች በሚገኙ ዜጎች የተናጠል መስዋዕትነትም ሆነ በአንዳንድ ቅን-አሣቢ ዴሞክራት ወገኖች የተናጥላ ሙከራ እንደ-ኢሕአዴግ መሪዎች ያሉ ጨካኝ አምባ-ገነን ገዥዎችን አቅጣጫ ማስቀየርና ሠፊውን ሕዝብ መታደግ የማይቻል የመሆኑ ጉዳይ ነው፡፡ የነጥቡ ጭብጥ ከእነዚኽን እብሪተኛ አምባ-ገነኖች ጋር የሚደረገው ሰላማዊ ትግል አገር-አቀፋዊና ሕዝባዊ እንዲሆን ቢደረግ የጋራው ትግል ሊሰምር የተሻለ ዕድል መኖሩ ብቻ ሣይሆን፤ መስዋዕትነቱ ሥርዓቱን ለመታገል ቆርጠው በተነሱ እንደ ደቡብ እና እንደ አምቦ በመሣሰሉ በአገሪቱ የተወሰኑ አካባቢዎች የሚኖሩ ዜጎች “ዕዳ” ሊሆንና የአገዛዙ በቀል-ያዘለ ጥሬ ጉልበት ውርጅብኝ ሰለባ አይሆኑም ነበር የሚል እንጂ የተከፈሉ መስዋዕትነቶችን ዝቅ በማድረግ፣ በመዘንጋትም ይሁን የሁኔታውን አስቸጋሪነት ባለማስተዋል አይደለም፡፡

መቸም በአሁኑ ጊዜ በደፈናው 'ሰላማዊ ትግል' በሚል መፈክር ሥር የተሰለፉ ወገኖች ነገሩን አቅልለውና አልፎም ግላዊ አድርገው በመውሰድ “እስኪ ናና ቅመሰው” ለማለት የሚቃጣቸው አይጠፉም፡፡ ግን እነኝኽን ወገኖቸን በአክብሮት የማሳስባቸው በመጀመሪያ የተናጠል ጥረታችሁ መልካም ነው፣ ሆኖም በምንም መልክ ይሁን በምን ማንኛውም ትግል መስዋዕትነትን እንደሚጠይቅና እንደሚያስከፍል አትዘንጉት፣ የተሻለ ማድረግ ትችላላችሁ፣ እናንተም ዋና ውስጥ ገብቶ ውሃ አይንካኝ (አትርጨብኝ) ዓይነት ካልሆነ በስተቀር የከፈላችሁትና የምትከፍሉት ክቡር መስዋዕትነት ገና በትግሉ ለመሰለፍ ስትወስኑ ያን እንደሚጠይቅና እንደሚደርስም ትዘነጉታላችሁ የሚል ግምት አይኖረኝም የሚል ነው፡፡ በዚኽ ሃያ ዓመታትን ባስቆጠረ ኢሕአዴጋዊ የግዛት ዘመን ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሏል፤ እየተከፈለም ነው፡፡ ገናም ይከፈላል፡፡ ጥያቄው በዚኽ ቀጣይ ትግል ምን ያኽል መስዋዕትነት ተከፈለ፣ አልተከፈለ የሚል ሣይሆን፤ ታጋዩ ሕዝብ የከፈለው መስዋዕትነት መጣኝ ውጤት አስገኝቷል ወይስ አላስገኘም? የሚል ነው፡፡ መልሱም ከሌላ ሣይሆን ከኢሕአዴግ ከአጥፊ መርኃ-እቅዶቹ ጋር በሥልጣን መቀጠሉና ከዚያም ጋር ተያይዞ ሕዝባችን ላይ እየወረደ ካለው ሰቆቃ ላይ ይገኛል፡፡ ስለዚኽ ነገሩን ከየግል ጥረት ወጣ አድርገን እስኪ ጉዳዩ ላይ የምር ግልጥ ውይይት ይደረግ፡፡ ከለውጥ ፈላጊው ውስጥ በሰላማዊ መንገድ እታገላለሁ የሚለው ወገን እስከ-አሁን በተቀጠለበት መንገድና በተያዘው የትግል ትልምና ስልት ለሕዝብ ጥያቄዎች አግባባዊ ምላሽ ሊሰጥ የሚችል አዎንታዊ ለውጥ ይገኛል ብሎ የሚያስብ ካለ በእጅጉ እገረማለሁ፡፡ (በዚኽ ነጥብ ላይ በመጨረሻው ክፍል እመለስበታለሁ)፡፡

ትግል፣ ያውም ለአገር አንድነትና ክብር፣ ለሕዝብ ሁለንተናዊ መብቶችና ሉዓላዊነት ከአምባ-ገነኖች ጋር የሚደረግ ትግል ውጤቱ የአምባ-ገነን አገዛዝን የጥፋት አቅጣጫ ማስቀየር የማይችልና እንዲያውም አልፎ-ተርፎ የሚያጠናክር ከሆነ ጥያቄው በማንኛውም

ኃላፊነት የሚሰማውና ጉዳዩ የሚያገባው ዜጋ መልሶ መላልሶ መነሣቱ ተገቢም ጤናማም ይሆናል። አዎን ለብሔራዊ (አገራዊ) አንድነትና ክብር፣ ለሕዝብ ሉዓላዊነት ባለፉት ሃያ ዓመታት ብቻ ብዙ መስዋዕትነት ተከፍሏል። ትንንቁም አልቆመም፣ ቦግ ስልምልም፣ ቀና ቀልበስ፣ ጠንከር ደከም፣ ቢልም አልቆመም፣ ሊቆምም አይችልም፣ አይገባምም። መቆም ሣይሆን በሾረ መልኩ መጠንከር ይኖርበታል። በሰላማዊ ትግል ስም እስከ-አሁን በአገራችን የታየው ትግል ምናልባት ለተወሰኑ ቡድኖች መሪዎች በልዩ ልዩ መልክ የሥራ ዋስትናና "በተቃዋሚው ክፍል መሪነት" መጠነኛ መታወቅን ያተረፈ ሊሆን ከመቻሉ ውጭ የሕዝቡን ትግል ወደ-ፊት በማስኬዱ ረገድ እርባና ያለው ውጤት አሰገኝቷል ማለት ያስቸግራል።

በትግል ትልምና ስልት ላይ በአባላት ዘንድ የሚኖር የግንዛቤ ፍልሰት አባል ድርጅቶች ሁሉ የጋራ ስምምነትን የጠበቀ አካሄድ እንዳይከተሉና ከጋራው ስብስብ እምነት ውጭ የሆነ፣ አልፎም ተፃራሪ አቋም እንዲያንፀባርቁና ያሻቸውን መንገድ እንዲከተሉ በር ስለሚከፍት የጋራ ጥረቱን አጨናጋፊና ድካሙን ሁሉ ከንቱ የሚያደርግ እንደሚሆን ለውጥ ፈላጊው ክፍል በተገቢ ሊያጤነው የሚገባ ጉዳይ ይሆናል። ከዚኽ የግንዛቤ ግድፈት ተንደርድሮ የሚደረግ ሰላማዊ ትግል ትርጉም-የለሽና የሕዝብን ጥያቄ በአግባቡ መመለስ አለመቻል ብቻ ሣይሆን ለአገዛዙ ምርኩዝ ከመሆን የማያልፍና ሕዝብ ለውጥን በቀቢፀ-ተስፋ እንዲጠብቅ፣ ታጋዩም በአጉል አነሁላይ የፖለቲካ ማዕበል ውስጥ እንዲላጋና አስፈላጊ ላልሆነ መስዋዕትነት እንዲዳረግ የሚያደርግ አመለካከት ነው የሚል እምነት አለኝ። የሆነ ሆኖ በቅድመ-ኢሰዴአኃ፣ በኢሰዴአኃም ሆነ ድኅረ-ኢሰዴአኃ ባሉና በተቃዋሚው ጎራ በተሰለፉ ኃይሎች በተለይም ከአገር-ውጭ እና በአገር-ውስጥ በሚገኙ (በአገዛዙ "ሕጋዊ" ፈቃድ በተሰጣቸውና በአገሪቱ ውስጥ በግልጥ ለመንቀሳቀስ "ሕጋዊ" ፈቃድ በሌላቸው ድርጅቶች) መካከል በዚኽ ዓብይ ጉዳይ ላይ አሁንም አጠቃላይ የጽንሰ-አሣብና የግንዛቤ መጣጣም የለም ማለት ይቻላል። በዚኽ የሰላማዊ ትግል ፍልሥፍናና አተረጓጎም ላይ በድርጅቶች መኻል ሙሉና ግልጥ መግባባት አለመደረሱና የጠራ ግንዛቤ አለመኖሩም በለውጥ ፈላጊው ክፍል ለተከሰቱ አለመጣጣሞችና ለልዩነቶች ምንጭ ከሆኑት ነጥቦች ውስጥ አንደኛው እንደሆነም በተደጋጋሚ የታየ ጉዳይ ነው። ይኽ ግዙፍ የግንዛቤ ዝንፈትም ለውጥ ፈላጊው ክፍል በሚነድፋቸው የትግል ትልሞችና ስልቶች ላይ ከፍተኛ ደንቃራ እንደሆነና ለሰላማዊ ትግሉ ግብ አለመምታትና ለሕዝባችን ሰቆቃ መቀጠል ከመሪ ብሔራዊ ድርጅት እጥረት ጋር ተዳምሮ ዋና ተጠያቂ እንደሆነ ግልጥ ይመስለኛል።

የኢሰዴአኃ ምክር-ቤትም በሁሉም አባላት ዘንድ የተቀየሰው የትግል ትልም ላይም ሆነ ትግሉ የሚጠይቀው መራር መስዋዕትነት ላይ ከደፈናዊ ስምምነት ባለፈ የጠራ ግንዛቤና ተገቢ መግባባት ሳይያዝ ነው ሕአዴግን ለመፋለም የተነሣው። ምክር-ቤቱ እከተለዋለሁ ባለው ሰላማዊ ትግል ላይ ያ ብዥታ እንዳለ ነው እንግዲኽ አንዴ ለአዲስ የሽግግር ሂደት ሁኔታን ለማመቻቸት እንዲቻል የተቃዋሚው ጎራ በሕዝብ ዘንድ ተቀባይነትና ተኣማኒነት ያለው የተጠናከረ ትግል ለማድረግ ኃይሎችን ማሰባሰብ እንደ-ግብ፣ ሌላ ጊዜ የውስጥ ኃይል ባልደረጀበት፣ የግንዛቤ ጥራትና ትግሉን ለመምራት የሚጠይቀው ተኣማኒነት ያለው ጠንካራ ማዕከላዊ አመራር ክፍተት ባለበት፣ ለሠፊው ሕዝብ ቀርቶ ለአባል ድርጅቶች በበቂ ግልጥ ባልሆነና ጥልቅ ውይይትና መግባባት በሌለበት ሁኔታ ከሽግግር መንግሥቱ ጋር መደራደር፣ ወዘተ... በሚል የጠራ ፈር ሣይጨብጥ ፈታኙን ሰላማዊ ትግል ለማድረግ የተውተረተረው። በኢሰዴአኃ በኩል ከኢሕአዴግ ዓይነት አምባ-ገነናዊ የአገዛዝ ሥርዓት ጋር ወሳኝ ትግል ለማካሄድ በቅድሚያ የትግሉን ልዕለ-ግብ በትክክል በተረዱና ለትግሉ ትርጉም ያለው አስተዋፅዖ ማድረግ በሚችሉ፣ የጎላ እርባና ባላቸው ክፍሎች መኻል የትግሉ ትልምና ስልት ላይ ግልጥ መግባባት አለመኖሩ፣ ከእነዚኽ ክፍሎች ውስጥ ለጋራ ውሳኔዎች ተግባራዊነትና ለዚሁ መተክል እውን መሆን ለሚጠይቀው መራር ትግል ተኣማኒነት ያለው ማዕከል የሚሆኑበት ሁኔታ አለመመቻቸቱ፣ የተያዘው ሰላማዊ ትግል ሕዝባዊ መሆን እንደሚኖርበትና ያ ደግሞ ምንን እንደሚጠይቅ በሁሉም አባላት ዘንድ በትክክል ግልጥ ያልነበረና ሙሉ መግባባት ያልነበረበት ሁኔታ መኖሩ፣ ወዘተ... የምክር-ቤቱን ትግል ከጅምሩ በእጅጉ ስንኩል እንዲሆን እንዳደረገውና ለውድቀት እንደዳረገው ግልጥ ነው።

***በክፍል አሥራ-አንድ ይቀጥላል......***